# በቤተሰብ ፡ ሕግ ፡ አንድ ፡ ፕሮብሌም ።

በካተሪን ፡ አዶኖቫን ፡*

የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔትን ፡ የሚያነቡ ፡ ለሚቀጥሉት ፡ ጥያቄዎች ፡ የተሟሉ ፡ መልስ ፡ ለመጽሔቱ ፡ በመስጠት ፡ የሕግ ፡ ዕውቀታቸውንና ፡ ለሕጋዊ ፡ ጥያቄዎች ፡ መልስ ፡ የመስጠት ፡ ችሎታቸውን ፡ እንዲገምቱ ፡ (እንዲፈትኑ) ፡ ተጋብዘዋል ። በአማርኛም ፡ ሆነ ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ተጽፎ ፡ ለመጽሔቱ ፡ የተሰጠና ፡ ብልጫ ፡ ያሳየው ፡ መልስ በመጽሔቱ ፡ ዘጠነኛ ፡ እትም ፡ ፪ኛ ፡ ቮልዩም ፡ ላይ ፡ ይወጣል ። መልሶቹ ፡ ከሚያዝያ ፡ ፯ ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ መሰጠት ፡ አለባቸው ። መልሱ ፡ ለእትም ፡ የተመረጠለት ፡ ተካፋይ ፡ አንድ ፡ መልሱ ፡ የሚወጣበትን ፡ መጽሔትና ፡ አምስት ፡ የመልሱ ፡ ሌላ ፡ እትሞችን ፡ በነፃ ፡ ይወስዳል ።

## ፕሮብሌም ፡

ስለ ፡ መጥፋት ፡ የሚናገር ፡ ምዕራፍ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። አንድ ፡ ሰው ፡ የጠፋና ፡ ቢያንስ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ወሬው ፡ ያልተሰማ ፡ እንደሆነ ፡ መጥፋቱ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊነገር ፡ (ሊገለጽ) ፡ ይችላል ። በቁጥር ፡ ፩፻፺፫ ፡ (፩) ፡ መሠረት ፡ የመጥፋቱ ፡ መገለጽ ፡ በጠፋው ፡ ሰው ፡ ጋብቻ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ውጤት ፡ የጋብቻው ፡ መፍረስ ፡ ይሆናል ። ቢሆንም ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፺፫ ፡ የሚከተሉትን ፡ ንዑስ ፡ ቁጥሮች ፡ ይይዛል ።

“(፪) የመጨረሻዎቹ ፡ ወሬዎች ፡ ከተሰሙበት ፡ በኋላ ፡ የተፈጸመውን ፡ የወንዱን ፡ ወይም ፡ የሴቲቱን ፡ ጋብቻ ፡ ጠፋ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ ካልሆነ ፡ ሊቃወመው ፡ የሚችል ፡ የለም ።

(፫) ነገር ፡ ግን ፡ ክሱ ፡ በተጀመረበት ፡ ቀን ፡ የጠፋው ፡ ሰው ፡ በሕይወቱ ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ በማያከራክር ፡ አኳኋን ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ያረጋገጠ ፡ እንደሆነ ፡ ጋብቻውን ፡ ሊቃወመው ፡ ይችላል ።”

ዶክተር ፡ ቫንደርሊንደን ፡[1] ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ (፪)ን ፡ በመጥፋት ፡ በሚሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ምክንያት ፡ የፈረሰው ፡ ጋብቻ ፣ ምንም ፡ እንኳ ፡ ቀሪው ፡ ተጋቢ ፡ እንደገና ፡ ቢያገባም ፤ የጠፋው ፡ ሰው ፡ በተመለሰ ፡ ማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ እንደገና ፡ ሊመሠረት ፡ ይችላል ፡ የሚል ፡ ትርጉም ፡ ይሰጠዋል ። ስለዚህም ፡ የሁለተኛው ፡ ጋብቻ ፡ መጽናት ፡ ምንጊዜም ፡ አጠራጣሪ ፡ ሆኖ ፡ ይቀርና ፡ የጠፋው ፡ ሰው ፡ ተጋቢ ፡ ሁልጊዜ ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻን ፡ ለመፈጸም ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ አስተያየት ፡ የጠፋው ፡ ሰው ፡ መመለስ ፡ ሁለተኛውን ፡ ጋብቻ ፡ እንደሌለ ፡ ከሚያደርገው ፡ ከፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ይመሳሰላል ።[2] የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ እንዱ ፡ ችግር ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፺፫ (፪) ፡ በንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ የተጠቀሙባቸውን ፡ “የመጥፋቱ ፡ ማስታወቅ ፡ ፍርድ ፡” የሚሉትን ፡ ቃላት ፡ ከመጠቀም ፡ ይልቅ ፡ “የመጨረሻዎቹ ፡ ወሬዎች ፡ ከተሰሙበት ፡ በኋላ” ፡ የሚሉትን ፡ ቃላት ፡ መጠቀሙ ፡ ነው ።

---

* የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፤ ቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ ።

1. ጄ. ቫንደርሊንደን ፤ ዘ ፡ ሎው ፡ ኦፍ ፡ ፊዚካል ፡ ፐርሰንስ ፤ ገጽ ፡ ፻፳፫ ።
2. ኤም ፡ ፐላንዮል ፡ ኤንድ ፡ ጂ ፡ ሪፐርት ፤ ትሬይት ፡ ፕራቲክ ፡ ደ ፡ ድሮዋ ፡ ሲቪል ፡ ፍሮንሴ ፤ ቮልዩም ፡ ፩ ፤ ገጽ ፡ ፶፭ ።

ነገር ፡ ግን ፡ በይበልጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ችግር ፡ የሚፈጥሩት ፡ ስለመፋታት ፡ የሚናገሩት ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፳፱ና ፡ ፯፻፰ ፡ ናቸው ። በቁጥር ፡ ፯፻፳፱ ፡ (ለ) ፡ መሠረት ፡ "ከባልና ፡ ሚስት ፡ ከሁለቱ ፡ አንደኛው ፡ ከሚኖሩበት ፡ ቤት ፡ ጠፍቶ ፡ ስለሄደ ፡ አጅግ ፡ ቢያንስ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ያለበትን ፡ ስፍራ ፡ አንደኛው ፡ ሳያውቅ ፡ የቆየ ፡ እንደሆነ ፡" ከባልና ፡ ሚስት ፡ አንዱ ፡ ሊጠቀምበት ፡ የሚችል ፡ ከባድ ፡ የመፋታት ፡ ምክንያት ፡ ይኖረዋል ። እንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ መፋታት ፡ በንብረት ፡ (በገንዘብ) ፡ ላይ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ ለቀሪው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ የሆነውን ፡ በሙሉና ፡ ከጠፋው ፡ ሰው ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ሦስተኛው ፡ መስጠት ፡ ነው ። በቁጥር ፡ ፯፻፰ ፡ (ለ) ፡ መሠረት ፡ "ከባልና ፡ ሚስት ፡ ያንደኛው ፡ ከአገር መጥፋት ፡ በፍርዱ ፡ ውሳኔ ፡ ተገልጾ ፡ እንደሆነ ፡" ጥፋት ፡ ሳይኖር ፡ ለመፋታት ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ይኖራል ። የእንደዚህ ፡ ዐይነቱ ፡ መፋታት ፡ ውጤት ፡ የጋራ ፡ ሀብቱን ፡ እኩል ፡ የመካፈል ፡ ይሆናል ።[3]

<u>ጥያቄዎች ፤</u>

፩) በቁጥር ፡ ፯፻፰ ፡ (ለ) ፡ መሠረት ፡ የተገኘው ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ (መፋታት) ፡ በቁጥር ፡ ፩፻፳፫ ፡ (፪)ና ፡ (፫) ፡ ተቃውሞ ፡ ሊነሣበት ፡ ይችላል ፡ ወይ ?

፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በቁጥር ፡ ፯፻፲፱ ፡ (ለ) ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ (አቤቱታ) ፡ በሚያጋጥመው ፡ ጊዜ ፡ ጉዳዩ ፡ የመጥፋት ፡ (absence) ፡ ወይም ፡ ከሚኖሩበት ፡ ቤት ፡ ጠፍቶ ፡ የመሄድ ፡ (desertion) ፡ መሆኑን ፡ የሚወስነው ፡ እንዴት ፡ ነው ? (በይበልጥ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ ገንዘብ ፡ ነክ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከተሰጡዋቸው ፤ ማሰብ ፡ የሚችሉ ፡ ባሎች ፡ ወይም ፡ ሚስቶች ፡ በሙሉ ፡ ከሚኖሩበት ፡ ቤት ፡ ጠፍቶ ፡ በመሄድ ፡ (desertion) ፡ የሚገኘውን ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስን ፡ አይመርጡምን) ?

፫) ቁጥር ፡ ፩፻፳፫ ፡ (፪) ፡ መጥፋትን ፡ የሚገልጽ ፡ ፍርድ ፡ ያልተገኘበትን ፡ ጉዳይ፡ ይመለከት ፡ እንደሆነ ፡ ይህ ፡ ጥያቄ ፡ ወይም ፡ ጉዳይ ፡ በቁጥር ፡ ፯፻፲፪ ፡ በሚገባ ፡ አልተሰጠምን ፡ (ንዑስ) ፡ ቁጥር ፡ (፪) ፡ "ክሱ ፡ ከተመሠረተበት ፡ ጊዜ" ፡ በሚለው ፡ ፈንታ ፡ "ጋብቻው ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡" የሚለውን ፡ በማመልከቱ ፡ ጉድለት ፡ ቢኖረውም ፡ እንኳ) ?

፬) በሶቪየት ፡ ሕግ ፡ የጠፋው ፡ ሰው ፡ መመለስ ፡ በቀሪው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት፡ ተከታይ ፡ ጋብቻ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ውጤት ፡ እንደሌለው ፡ አስታውስ ።[4] የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ እንዲኖረው ፡ የሚገባ ፡ አስተሳሰብ ፡ ይህ ፡ መሆን ፡ አይኖርበትምን ?

---

3. ቁጥር ፡ ፩፻፲፪—፶፬ ፡ ክም (Cum) ፲፱፻፷፬(፩)
4. ሬቪው ፡ ኢንተርናሲዮናሌ ፡ ደ ፡ ድሮዋ ፡ ኮምፓሬ ፡ (፲፱፻፶፱) ፤ ገጽ ፡ ፫፻፶፬ ።